የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ
(ወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር፣)
መብትና ጥቅም
የሚታገል ጋዜጣ

ቁጥር 71 ህዳር 30/1972

ኢማሌድህ፣ ከአብዮታዊ መዓከል ወደ ፀረ አብዮት መዓከል

ባለፈው ቁጥራችን ኢማሌድህ ከህብረት ወደከስረት ስላደረገው ጉዞ አትተናል:: በእትሙ ውስጥ ኢማሌድህ የተመሠረተበትን የፕሮግራምና የመርሃ ግብር መድረክ ከከዳ በኋላ፣ ድርጅታዊ ከስረት ደርሶበት ምንሸርሸረ ቢወጣ ምንም እንደማያስደንቅ ገልፀን ነበር:: እንደዚያ የከሰረው ኢማሌድህ፣ የወዝአደሩን ፓርቲ ለመመሥረት ብቃትና ጥራት ያለው አብዮታዊ መዓከል መሆኑ ያከተመው፣ ኢማሌድህ ከተመሠረተበት ፕሮግራምና መርሃ ግብር መንሸራተት በጀመረበት ጊዜ ነው:: ታዲያ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ደጋግመን እንዳልነው ደግሞ፣ "ኢማሌድህ ይዘት በነበረው የከስረት ጉዳና ቀጥሎ፣ ወደውህደት ተሸጋገርኩኝ፣ "የሠራተኛ ፓርቲ" ተመሠረተ" ቢል ኑሮ እንኳን፣ የኢትዮጵያ አብዮታዊያንና ግንባር ቀደም ወዝአደሮች አቋም ገልፀ ነበር:: ከከሣራ "ህብረት" የሚፈልቀውን ከሣራ "የሠራተኛ ፓርቲ" በምንም ዓይነት እንደማይቀበሉት ደጋግመው ያስታወቁት ጉዳይ ነበር::

ብቻ አንዱ አሳዛኝ ፊሊጥ ካለቀለት በኋላ፣ ሌላ የባሰ አሳዛኝና ምስኪን ፊሊጥ መስማት የተደጋገመው ልምዳችን የሆነው እና የኢትዮጵያ አብዮታዊያንና ግንባር ቀደም ወዝአደሮች፣ አሁን ደግሞ "አብዮታዊ መዓከል" ከእንገዲህ በገለሰብ "ኮሚኒስቶች" ውህደት "እንደሚለመልምና እንደሚያብብ" ሰማን:: በዚህ ያገባኛል የሚለውም ሁሉ፣ ከአንድ "ኮሚሽን" ከተባለ ስመ ጥሩ የማጣሪያና የምለመላ ቢሮ እየሄደ እንዲጣራ ሰፊው ህዝብም፣ "ኢማሌድህ ጥንስሱ ሳይፈላ ተደፋ" እያለ ገና በመተቸት ላይ ነበር:: አሁን ገን፣ "እሱን ተወው፣ ሌላ ጥንስስ እየተበካ ነው" ተብሎ ተነገርታል:: ያባቶች ተረት ትዝ እያለው፣ "ገረም ጥንስስ ሳይከካ ተበካ" እያለ ነው::

እስቲ ደግሞ ይሄንን "አብዮታዊ" መዓከል እንመልከተው:: ለዛሬው "በህብረት ድምፅ" መጽሔት ቁጥር አምስትና ስድስት ላይ ብቻ ተወስነን እንቀጥላለን:: ይሁን እንጂ ወደ ሃተታው ከመግባታችን በፊት ደግሞ፣ አንባቢው ከዚሁ መጽሔት ወስደንና በተራ ቁጥር እየለየን ከዚህ በታች የምንጠቅሳቸውን አቋሞች ልብ ብሎ ይመልከታቸውና የራሱን ፍርድ ይስጥ::

1/ ስለ "ህብረት"

ሀ. ""የህብረት" አባሎች ሆነው የቀሩት ሶስቱ "ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች /ማሌሪድ፣ ሰደድና የወዝ ሊግ/ እስካሁን በርካታ የአብዮቱን ግንባር ቀደም ጥያቄዎች አበጥረውና አንጠርጥረው በመመርመር የሚያመርቁ የአንድነት አቋሞች ላይ ለመድረስ አስችሏቸዋል::" /ህብረት ድምፅ ቁ.4 ገፀ 32፣ ሚያዚያ 1970/:: "የዛሬው የህብረቱ የጋራ መግለጫ የህብረቱን እድገትና ጥንካሬ ... የህብረቱ አባሎች የሆኑትን የሶስቱን ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች /ማሌሪድ፣ ሰደድና ሊግ/ የርዕዮተ ዓለም አንድነት የሚያረጋግጥ ነው::" /የመሸጋገሪያ ወቅት የጋራ መግለጫና የድርጊት ፕሮግራም፣ ሰኔ 1970/

ለ. "ይህ በጉ አዝማሚያ ሲሆን፣ በዚያው ሰሞን ኢማሌድህ ውስጥ አንድ ያልተጠበቀ /?/ አዲስ ሁኔታ /?/ ተከሰተ:: ... አድሃሪያን በድርጅቶች ውስጥ በገፍ ተሰገሰገው አብዮታዊያንን ለማመስ እድል በማግኘታቸው የውህደት ጉዳይ እየመነመነ መምጣቱ በተጨባጭ ታይቷል::" /"የህብረት ድምፅ" ቁ.5 ገፀ13፣16፣ የካቲት 1971/

2/ ስለ መዓከል

ሀ. ""የአብዮታችንን ሂደት ስንገመግመው፣ ትግላችን ዛሬም የሚጎድለው አቢይና ወሳኝ ነገር አለ:: ዛሬም በአንድ አስተማማኝ ዘላቂ መዓከል ለመመራት አልበቃም::" /"የህብረት ድምፅ" ቁ.5፣ ገጽ 4 የካቲት 1971/

ለ. "ለአብዮቱ አንድ ማዕከል ማስገኘት አማራጭ የሌለው መሆኑን በመገንዘብ ኢማሌድህን መሥርተዋል::" /"የህብረት ድምፅ" ቁ.5፣ ገጽ14፣ የካቲት 1971/

ሐ. "ወሳኝ በሆኑ ጥያቄዎች ላይ ስምምነት ተደርሷል:: እነዚህም...25/ አብዮቱ ከተቀጣጠለበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁንም ማዕከል እንደነበረው፣ ይህም መዓከል ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ እንደነበረና እሱም አብዮታዊ መሆኑን" /"የህብረት ድምፅ" ቁ.5፣ ገጽ 16፣ የካቲት 1971/

3/ <u>ስለወዝአደሩ ፓርቲ አፈጣጠር</u>

ሀ. "ሰፊው ሕዝብ አስተማማኝ መሪ የወዝአደሩ ፓርቲ ይመሠረት ይላል:: የዚህም ገንባር ቀደም መሪ ዕውን መሆና ብቸኛ ዘዴ በአገሪቱ ያሉት ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ህብረት መፈጠርና በትግል መዋሃድ መሆኑንም ጠንቅቆ በማወቁ ያላንዳች መታከት "ኢማሌድህ ይጠንከር" እያለ ያስተጋባል:: /"የህብረት ድምፅ" ቁ.4፣ ገጽ 31-32፣ ሚያዝያ 1970/

ለ. "የወዝአደሩን ፓርቲ ለመፍጠር 'ብቸኛው ዘዴ" በአገሪቱ ያሉትን ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ህብረት መፍጠርና በትግል ማዋሃድ ሳይሆን፣ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮተ ዓለም የታጠቁትን እውነተኛ ታጋዮች በማዋሃድ ነው" /"የህብረት ድምጽ" ቁ.5፣ ገጽ 16፣ የካቲት 1971/

እዚሁ ላይ እናቁም:: ከከሣራው ኢማሌድህ ጽሑፎች ውስጥ እንዲሁ እንደዚሁ እያለን መዓት እርስ በራሳቸው የሚቃረኑ አቋሞችን ልንጠቅስ እንችላለን:: እነዚህና ቸማ ውልክፍክፋቸው የሚወጣው ከመስመር መስመር ነዉ:: ለናም መጥኔውን ይስጠን እንጅ፣ የፖለቲካ ክሥረት የተጠናወጠው ድርጅት እንዲሁ "ኑሮ" ብሎ የያዘውን ቀዝት የሚገፋው እየተጠነጋገረ ነው:: ይሁንና፣ ታዲያ ምን ፍርድ እንስጠው!

"አብዛኛውን ጊዜ ቀኞች የሚናገሩትና የሚሠሩት፣ የሚፅፉትና ወደተግባር የሚተረጉሙት ሁሉ ለየቅሉ ነው:: በተለይም የወዝአደሩን ፓርቲ ጥያቄ በሚመለከተው ጉዳይ ላይ ደበስባሳና ሙልጭልጭ ያለ አቋም መውሰዱና በተለያዩ ጊዜያት በልዩ ልዩ ጽሑፎቻቸው እንደአሰሰተ የሚቀያየሩ መንደርደሪያዎች እንደነበራቸው የቀኞችን ልሳን የተከታተለ ሃቀኛ ተራማጅ ሁሉ በትክክል ሊገነዘበው ይገባል::"

አንባቢው "መኢሶን ደግሞ ይሄንን የጻፈው መቼ ነው?" ብሎ ይጠይቅ ይሆናል:: የለም ይህንን የፃፈው መኢሶን አይደለም:: የነዚህ የብልህ አረፍተ ነገሮች ባለቤት አብዮታዊ ሰደድ ቁ.17 ነው:: ታዲያ አብዮታዊ ሰደድ ይህንን የፃፈው "ቀኝ መንገደኛውን" መኢሶንን ለማጋለጥ በማለት ነበር:: ብቻ እናም ብንሆን ምንም አንጨምርበትም:: አንባቢው ከዚህ በላይ ከኢማሌድህ ጽሑፎች ውስጥ የጠቀስናቸውን እንደገና ተመልሶ እንዲመለከታቸውና እንዲያነፃፅራቸው በድጋሚ ጋብዘነው እናልፋለን:: ብቻ፣ እዚሁ ላይ ደግሞ፣ ከኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች የትግል ታሪክ ውስጥ አንድ የርዕዮተ ዓለም ገብ ገብ ምዕራፍ ትዝ አለንና፣ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም የሚነግዱ አድርባይ ኃይሎች እንደምን እንደሁለት ጠብታ ውሃ እንደሚመሳሰሉ ስንመዘግብ እጅግ መደነቃችንም እንዳልቀረ አንባቢን ሳናስታውሰው አናልፍም::

በ1966 ዓ.ም. ነው:: አንድ የኢህአፓ ገለገል ድርጅት ሆኖ በውጭ ሃገር የተቋቋመ "ፌዴሬሽን" የሚባል ትርምስምስ ድርጅት ነበር:: ይኸም ድርጅት "ቡሌቲን" የተባለ ጋዜጣ ያወጣ ነበር:: ታዲያ፣ ስምንት የሚሆኑ "የቡሌቲን" ጋዜጣውን እትም ያወጣል:: በዓመቱ መጨረሻ ላይ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ጉባዔ ተደረገና፣ የማህበሩ ሃቀኛ ታጋዮች "የቡለቲንን" ጋዜጣ ቁጥር በቁጥር እየወሰዱ:- "ቁጥር አንድ እንደዚህ ብሎ ነበር፣ ቁጥር ሁለት ደግሞ እንደዚህ ይላል፣ ቁጥር ስስት ደግሞ..." እያሉ በየእትሙ የተለያዩ አቋሞችን እንደወሰደ በማጋለጥ ገንጥለጥሉን ሲያወጡት፣ አንዱ ነገሩ የገባው ከመሃል ብድግ አለና፣ "ምን ቁጥር አንድ ቁጥር ሁለት እንላለን አቋም አንድ አቋም ሁለት... እንበል እንጂ" በማለት ተቸቶ፣ ሰውን ሁሉ በሳቅ ጨረሰው:: እናም ዛሬ፣ "የህብረት ድምጽን" ቁጥሮች ስናገላብጥ፣ ምን "ቁጥር" አስጠቀሰን፣ አቋም አንድ አቋም ሁለት እንበል እንጅ ማለታችን አልቀረም:: አዎን በማርክሲዝም የሚነግዱ አድርባዮች ምንጊዜም እንደዚሁ ናቸው::

ደግሞስ ካርል ማርክስ የቱን ያህል ዕውነት አለው? ካንድ ቦታ ላይ እንዲህ ይላል:- "ታሪክ ራሱን ይደግማል ሲል ሄገል ዕውነት አለው:: ይሁንና ሄገል የረሳው ነገር ታሪክ ራሱን ሲደግም ለመጀመሪያው ጊዜ እንደአሳዛኝ ድራማ ነው:: ለሁለተኛው ጊዜ ደግሞ እንደ አስቂኝና መሳለቂያ ትርዒት ነው::"

ይልቁና አሁን፣ ምንጊዜም ወዳልተደበሰበሰውና ወዳልተመለጨለጨው አቋማችን እንመለስና ደጋግመን ያልነውና የፀና አቋማችንን እንደገና እንገልፀው:: ስንት መዓት ጓዶቻችንን የሰዋንበትን አቋማችንን እንደገና እንገልጸው::

የወዝአደሩ ፓርቲ እንደዚሁ በአቦ ሰጡኝ የሚፈጠርና የሚሰየም ነገር አይደለም፡፡ የታወቁና አጠቃላይ የሆኑ ጠባዮች አሉት፡፡ አጠቃላይ የሆኑ የአመሠራረት ሂደቶች አሉት፡፡ ፓርቲው በፖለቲካ ብስለቱና ንቃተ የመጠቁና የላቀ የወዝአደሩ ግንባር ቀደም መሪ ድርጅት ነው፡፡ የሚያስተሳስረውና የሚያቅፈው በትግል ልምዳቸውና በንቃታቸው፣ በአብዮታዊ ወኔያቸውና በተለይም የግል ጥቅማቸውን ከደው ለወዝአደሩና ለጠቅላላው ጭቁን ህዝብ ቆመው በግንባር ቀደምትነት ለመታገል ባላቸው ዓላማ፣ ፍላጐትና ችሎታ የፀኑትን ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ነው፡፡ እንደዚሁም በሚያሳዩት ዲሲፕሊን ሁሉ ለቀውና መጥቀው የሚገኙትን፣ በታጋይነታቸውና በታታሪነታቸው፣ በሃቀኝነታቸውና በአብዮታዊ ትህትናቸው ከሰፊው ህዝብ ጋር የተዋሃዱትን፣ የሰፊውን ህዝብ አክብሮት፣ ድጋፍና ተደማጭነት ያገኙትን አብዮታዊያን ነው፡፡ እያን "የሚናገሩትና የሚሠሩት፣ የሚጽፉትና ወደተግባር የሚተረጉሙት ሁሉ ለየቅሉ" ሲሆን "በተለይም የወዝአደሩን ፓርቲ ጥያቄ በሚመለከተው ጉዳይ ላይ ደበስባሳና ሙልጭልጭ ያለ አቋም" ሲወስዱ፣ "በተለያዩ ጊዜያት እንደ እስስት የሚቀያየሩ መንደርደሪያዎች" ሲናራቸው፣ የዚህ ቢጤዎች "የሠርቶ አደሩን ፓርቲ" የሚያክል ነገር እንኳን ለመመሥረት "ለመጠንሰስም" እንደማይበቁ የዚያኑ ያህል ዕውነት ነው፡፡

እንደዕውነቱም ከሆነ፣ በዚህ የወዝአደሩ ፓርቲ መሠረታዊ ጠባዮች ላይ ብዙም መቀየት አያስፈልገንም፡፡ ይህ ጉዳይ ባለፉት ዓመታት ውስጥ በሰፊው ተብራርቷል፣ ተገልጿል፡፡ የኢትዮጵያ አብዮት በአፍላነት ይገሰግስ በነበረበት ወቅት፣ በህጋዊ መድረኮች ላይ ይወጡ የነበሩትን "የአብዮታዊት ኢትዮጵያን" መጽሔት ቅጾች፣ የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤትና የፖለቲካ ት/ቤት ያቀርቧቸው የነበሩትን የጥናትና የምርምር ጽሑፎች፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ይታተሙ የነበሩትን ክርክሮችና ውይይቶች፣ "በአዲስፋና" መጽሔት ላይ ይወጡ የነበሩትን ጽሑፎች፣ "ዓለም አቀፍ አሳታሚያች" ያሳተሟቸውን ጽሑፎች፣ እያን ከነዚያም ባሻገር ኢማሌድህ ራሱ የተመሠረተበትን የጋራ መግለጫና መርሃ ግብር ዘወር ብሎ ማየት ብቻ ይበቃል እንላለን፡፡ በነዚህ መድረኮች ላይ የተደረጉት ገለጣዎች ዛሬም ህያውና ትክክል ስለሆኑ፣ አንባቢን ወደነሱ ጽሑፎች ጋብዘነዉ ለማለፍ እንችላለን፡፡

የወዝአደሩን ፓርቲ አፈጣጠር በሚመለከተውም በኩል፣ እንደዚሁ በተደጋጋሚ የተገለጹ መሠረታዊ ሃቆች አሉ፡፡ የወዝአደሩ ፓርቲ ከወዝአደሩ የሙያ ንቅናቄና በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ከታነጹ አብዮታዊያን ውህደት የሚወጣ ግንባር ቀደም ድርጅት ነው፡፡ ጥቂት ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን የተቀበሉ "አብዮታዊያን ነን" ባዮች ተጠራርተው "የሠራተኛው መደብ ፓርቲ" አይሆኑም፡፡ የወዝአደሩ የሙያ ንቅናቄ ብቻውን የወዝአደር ፓርቲን አይወልድም፡፡ ደግሞም፣ መቼም "ለቸርነት ምንም አይሳነውምና"፣ ይህቺ ታሪክና ምድራችን ያበቀለቻቸው "ኮሙኒስቶች"፣ "የወዝአደሩን ፓርቲ በማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ህብረትና ውህደት ለመመሥረት እንደማይቻል ተደርሶበታል፡፡ ሳይንሳዊው ጉዳና 'ታጋዮችን' ማዋሃድ ነው" እያሉ "ሳይንሱን" ሲያዥጎደጉዱት ለመስማት በቃን እንጂ፣ የወዝአደሩ መደብ ፓርቲ በዚህ የግለሰብ "ታጋዮች" ውህደት ሲመሠረት ሰምተንም ዓይተንም አናውቅም ነበር፡፡

በየትኛውም አገር እንደታየው፣ በዚህ የወዝአደር ፓርቲ አፈጣጠር ሂደት ውስጥ፣ በመጀመሪያ ብቅ ብቅ የሚሉት ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን የተቀበሉ ትናንሽ ቡድኖችና ድርጅቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ቡድኖች በመጀመሪያው ላይ ርዕዮተ ዓለሙን ለማስፋፋት በተለያዩ መንገዶች ይታገላሉ፡፡ እንደዚሁም፣ ከነርሱ ቁጥጥር ውጭ በሚካሄደውና በሚያድገው የወዝአደር የሙያ እንቅስቃሴ ውስጥ እየገቡ በወዝአደሩ የኢኮኖሚና የነፃነት ትግል ይሳተፋሉ፡፡ የወዝአደሩን መደብ በተግባር ይዋሃዱታል፡፡ ቡድኖቹ ለየቅል የሚያደራጁት እነርሱ ፈልገው ሳይሆን፣ ከነርሱ ቁጥጥር ውጭ የሆኑ ሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎች በመኖራቸው ነው፡፡ ያም ሆኖ ይህ፣ እነዚህ ለየቅል በነፃ የተደራጁት ድርጅቶች በትግሉ ሜዳ መተዋወቃቸው አይቀርም፡፡ ነገሩ ተፈጥሮዋዊ ስለሆነ፣ በመሃከላቸውም ታክቲክና አስትራቴጂን፣ የፖለቲካና የአይዲዮሎጂ ጥያቄዎችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የመሥመር ትግል እያካሄዱ ይተባበራሉ /ህብረት/፡፡ ከዚያም ይዋሃዱና /ውህደት/ የወዝአደሩን ፓርቲ ይመሠርታሉ፡፡

ነገር ግን "ህብረታቸው" ህብረት የሚሆነው፣ "ከውህደታቸውም" የሠራተኛው ፓርቲ የሚመነጨው በመካከላቸው ያለው ግንኙነት ሁሉ በአኩልነትና በዲሞክራሲ መርሆዎች ላይ ፀንቶ ሲገነባ ነው፡፡ ማንኛውም ተባባሪ ድርጅት የበላይነትና ማንአህሎኝነት ሳይሰማው፣ ለመተባበር ፈቃደኛ የሆኑትን "ማርክሲስት ሌኒኒስት" ድርጅቶች ነፃ ህልውና ሲቀበልና ሲያከብር ነው፡፡ እንደዚሁም የትኛውም ድርጅት ቢሆን፣ መሠረታዊ ስምምነት የተደረሰባቸውን መሠረታዊ አቋሞች፣ ደንበር በጠለቀበት ቁጥር እየለወጠ "ከመሙለጭለጭና" ዓይን ካወጣ ክህደት ሲገታ ነው፡፡

በነዚህ ማርክሲስት ሌኒኒስት መርሆዎች ላይ የተባበሩት ማርክሲስት ሌኒኒስቶች፣ ወደውህደት ተሸጋግረው የወዝአደሩን ፓርቲ በቀላሉና በዕውነተኛ የአብዮታዊ ጓድነት መንፈስ ይመሠርተታል፡፡ ከውህደታቸው ጋር በተያያዘም ሁኔታ፣ ከወዝአደሩና ከተቀሩት ጭቁኖች ትግል በግንባር ቀደምትነት በመዋሃድ ይህንኑ ግንባር ቀደምትነታቸውን በተግባርና በተጨባጭ ኑሮዋቸው ሁሉ እያስመሰከሩ ይጎለምሳሉ፡፡ ይዳብራሉ፡፡ ከዚህ ውጭ ሌላ የወዝአደር ፓርቲ፣ ከዚህ ውጭ ሌላ የአፈጣጠር ሂደት ፀረ አብዮት አቋራጭ ነው፡፡

በቻ እስከ " ቀናች" የሚናገሩትና የሚሠሩት፣ የሚጽፉትና ወደተግባር የሚተረጉሙት
ሁሉ ለየቅሉ ሆኖ ነው እንጂ፣ ከዚህ በላይ ያለነውንማ እነሱም በ" ህብረት ድምጽ"
ቁጥር 5 ላይ ከገጽ 14–15 ድረስ ሌኒንና ሆ ቺ ሚንን እየጠቀሱ እንደሚከተለው
" ተናገረውና ጽፈው" ነበር:—

"ይህን በውህደት ፓርቲ የማስገኘት ስልት፣ የሌሎች አገሮች አብዮታዊያንም
በአገባቡ ተጠቅመውበት ተግባር ላይ ያዋሉት በመሆኑ ተከከለናነቱ የሚያጠራጥር
አይደለም:: ለምሳሌ በሩሲያ በ1903 የጠራ የወዝአደር ፓርቲ ለመመሥረት
በሁለተኛው ጉባዔ ላይ የተገኙት የ26 ድርጅቶች ተወካዮች ነበሩ:: ምንም
እንኳን የድርጅቶቹ አቋም የተለያየና ውጥንቅጡ የወጣ ቢሆንም፣ በታላቁ ሌኒ
ንና በቆራጠና አብዮታዊያን ተጋድሎ በመጨረሻ የተፈለገውን ዓይነት አብዮታዊ
ፓርቲ ለመመሥረት ተቻሏል::"

"በቪየትናምም እንደዚሁ በ1929 ገደማ ሶስት ኮሙኒስት ድርጅቶች ነበሩ::
ነገር ግን በወቅቱ ከፈረንሳይ ቀኝ አገዛዝ አርነት ለመውጣት ይታገሉ የነበረት
ወዝአደሮችና ሌሎች አብዮታዊያን ኃይሎች፣ የግድ የአንድ መአከል አመራር ይሹ
ነበር:: ስለሆነም ሆ ቺሚን በኮሚኒስት ኢንተርናሽናል ተጠሪነቱ፣ የኮሙኒስት
ድርጅቶች ተወካዮች ሰብስቦ ለአንድነት ትግል ከተካሄደ በኋላ፣ እ.ኢ.አ.
የካቲት 1930 የቪየትናም ህዝብ አለኝታ የሆነውና "የቪየትናም ሠራተኞች
ፓርቲ" በመባል የሚታወቀው ፓርቲ ህልወና አገኘ::"

እዚህ ላይ ምን ይጨመርበታል:: ምኑንስ " ለማድበስበስ" ይቻላል? ወዴትስ
"ለመሙለጥለጥ" ይቻላል? ሌኒንም ሆቺሚንም እንዳሉትና እንዳደረጉት የወዝአደሩ ፓርቲ
የሚፈጠረው "ከውህደትና" ለአንድነት በሚካሄድ ቀኝ፣ ሃቀኛ፣ ዲሞክራሲያዊና የእኩልነት
ትግል ነው:: ሆኖም፣ የኛዎቹ በለህና አስተዋይ "ሌኒኒስቶች" ይህንን ሁሉ ከፃፉ
በኋላ የሚደርሱበት መደምደሚያ ደግሞ፣ የሚከተለው ዓይን ያወጣ ሸፍጥ ነው:: እናንበው፣
"የኢትዮጵያ አብዮት ልዩ ባህሪይ የተገነዘቡና ከአብዮቱ ወገን ቆመው የሚታገሉ
የኢማሌድህ አባል ድርጅቶች /ሰደድ፣ ሊግ፣ ማሌሪድ/ የወዝአደሩን ፓርቲ ለማስገኘት
ድርጅትን ከድርጅት ጋር በጅምላ በማዋሃድ ሳይሆን፣ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮተዓለም
የታጠቁትን ዐውነተኛ ታጋዮች በማዋሃድ መሆኑን" አምነዋል:: /"የህብረት ድምጽ" ቁ.5
ገጽ 16/

በዚህ " በጅምላ ማዋሃድ" በሚለው ጥያቄ ላይ ወደኋላ እንመለስበታለን:: ከዚህ
በላይ ለጠቀስነው አንቀጽ ግን የሚከተለውን ተናገረን በቻ እንለፍ:: በዕውነቱ፣ በኢማ
ሌድህ አባል ድርጅትነት የቀረት " ሶስቱ" ድርጅቶች ይህንን ድፍረት የተመላበትና
ዓይን ያወጣ ሸፍጥ ሲጽፉ፣ ያለጥርጥር " ማንም የለብንም" በማለት ከፍተኛ የእብሪትና
የንቀት መንፈስ አድርባቸዋል:: ያለጥርጥር ደግሞ፣ የኢትዮጵያን ዕውነተኛ ማርክሲስት
ሌኒኒስቶች ገድለንና አስረን ጨርሰናል ብለው ተማምነዋል:: ይህ ሁሉ ካልሆነ ደግሞ፣
ለሥልጣን፣ ለክብርና ሞገስ የተያያዙትን እሽቅድምድም የዕውር የድንበራቸውን ሊገፉበት
ቆርጠዋል ማለት ነው:: ሌላ ምንም ፍቺ ሊኖረው አይችልም:: እናም፣ እኢዲስ " መገ
ገዱን ጨርቀ" አይሆንም ብለን እንተቻቸውና እንቀጥል::

ለመሆኑ ይሄ "የኢትዮጵያ አብዮት ልዩ ባህሪይ" እየተባለ የሚነገርለት ጉዳይ
ምንድን ነው? በኢትዮጵያ የወዝአደሩ ፓርቲ አፈጣጠር ሂደት እንዴት ነው?

የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ተወለደ የዛሬ አስራ አንድ ዓመት ወደ
ሃቀኛ የወዝአደር ፓርቲ መመሥረት፣ ወደ አርገጠናው የኢትዮጵያ ጥቁኖች ነፃ መውጣት
የሚወስደውን የመጀመሪያውን የማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅት መሠረት ጥሉ፣ የመላ ኢትዮ
ጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄን አቋቋሙ:: ዛሬ በትግሉ መስክ ላይ በተሰውት በነጓድ ደክተር
ከበደ መንገሻ፣ በነጓድ ዳንኤል ታደሰ፣ በነጓድ ደክተር ከድር መሃመድና በነጓድ መስፍን
ካሡና በእሥር ተይዘው በመሰቃቀ ላይ በሚገኙት በነጓድ ኃይሌ ፊዳ አርቀ አስተዋይ
አመራር ሥር፣ የኢትዮጵያን ወዝአደሮች ፓርቲ ለመመሥረት የሚያስፈልገው ሂደት በመኢሶን
ፕሮግራም ላይ በትከክል ተተለመ:: ሲፈጠር ጀምሮ ከአቀሙ በላይ መተንፈስ የማያውቀው
ድርጅታችን፣ በዚያን ሰዓት ጊዜያዊ ድክመቶችን ለራሱም ሆነ ለማንም አለሸሸገም::
ከሃቀኛ ወዝአደር ፓርቲ አፈጣጠር ሂደት አንፃር፣ ገና ብዙ የሚጎድሉት ነገሮች እንዳሉ
ያውቀ ነበር:: የመኢሶን ታጋዮች፣ በሃቀኝነታቸውና በቆራጥነታቸው እስከመጨረሻው ለመ
ጓዝ ባላቸው ፍላጎት ፀናታቸውን ምንጊዜም ቢሆን ተጠራጥረውት ባያውቁም፣ ከታሪክ ሂደ
ትና ከሰፊው ታጋይ ህዝብ ተሸቀዳደመው ራሳቸውን የወዝአደሩ ፓርቲ ብለው አለሰየሙም::

ምንም እንኳን መኢሶን ባንድ በኩል በጊዜው እሱ የሚባሉትን ማርክሲስት ሌኒኒስቶ
ችና ማርክሳዊ የጥናት ቡድኖች ከምላ ጉደል ያቀፈ ድርጅት ቢሆንም፣ ከማርክሲዝም መስ
ፋፋት ጋር ሌሎች ቡድኖች ለመሠረቱ እንደሚችሉ ተገንዝበና አውቀ ነበር:: ሌላው ቀርቶ፣
በዚያን ወቅትም ቢሆን እንኳን፣ ሌሎች የህቡዕ ድርጅቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ገምቶ ነበር::
ስለሆነም፣ በጊዜው ሊኖሩ ከሚችሉት የህቡዕ ቡድኖችም ሆነ፣ ገና የታሪክ ሂደት ሊፈጥራ
ቸው ከሚችሉቸው ሌሎች ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ከተቀበሉ ቡድኖች ጋር ሃቀኛ የሆነ የርዕዮተ
ዓለም ትግል አካሂደ ከነርሱ ጋር በመዋሃድ የሠራተኛውን ፓርቲ ለመፍጠር ራሱን ንቅናቄ
ብሎ ሰየመ::

ይህም ብቻ አይደለም:: መኢሶን በየካቲቱ ህዝባዊ አብዮታዊ አንቀሳቃሴ ወቅት
በስውር የነበሩትን ተራማጅ ድርጅቶችንና ቡድኖች ሁሉ ለማስተባበር እንዲቻል፣ ከነስሙ
"የተራማጅ ህብረት" የተሰኘን ጋዜጣ እያወጣ በመቀስቀስና በማወያየት ታግሏል:: ከዚህ
በኋላ፣ መኢሶን ኢማሌድህ እንዲመሠረት ያደረገው ተጋድሎና ከትግል ስልት ለውጥ በኋላ
ለተራማጆች ህብረት ያደረገው ቅስቀሳ የታወቁ ናቸው:: አሁን በነርሱ ላይ አንመለስም::
አንባቢን ወደ ሰሀዱ 67 መቁሙ ነው እናልፋለን::

በሌላ በኩል ግን የወዝአደሩን ፓርቲ ለመፍጠር አብዮታዊ ምሁራን ከወዝአደሩ የሙያ
ንቅናቄ ጋር መዋሃድ እንዳለባቸው የታወቀ ነገር ነው:: ይሁንና በጊዜው በወዝአደሩ
ውስጥ የመግባቱ ነገር ገና የመጀመሪያ ደረጃዎች ላይ ነበር:: ስለሆነም የኢትዮጵያ
ጭቁኖች በየመሥመሩና በየረድፉ ከሚያካሂዱት ዐለታዊ ትግል በሺህ በሚቆጠሩ ክሮች ሳይ
ተሳሰር በፊት መኢሶን ራሱን "የሠራተኞች ፓርቲ" ብሎ ለመሰየም አልፈለገም:: ይህ
አጉል መመፃደቅና በሠርቶ አደሩ ህዝብ ስም ለመነገድ ሆን ብሎ መነሳሳት በሆነ ነበር::
ባጭሩ መኢሶን ሲፈጠር ጀምሮ፣ ራሱን ለኢትዮጵያ ወዝአደሮች ፓርቲ እንደ አንድ አጠብ
ከመቁጠር አልፎ፣ ጣራም ግድግዳም ነኝ ብሎ አልቆጠረም:: ዐውነተኛ የወዝአደሮች ፓርቲ
እንዲፈጠር፣ የምንጊዜም ጥሪው የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ሁሉ በእኩል
ነት መድረክ ላይ ነፃና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እንተባበር፣ ከዚህ መድረክ ላይ
ተነስተን ሃቀኛውን የወዝአደር ፓርቲ እንፍጠር የሚለው ነው:: መኢሶን ሺህ ቢነገርበት፣
ሺህ ግፍ ቢፈፀምበት፣ በዚህ መላው ሃቀኛ ማርክሲስት፣ መላው ግንባር ቀደም ወዛደር፣
መላው አብዮታዊና አገር ወዳድ ምሁር፣ መለዮ ለባሽ፣ የጭቁን ብሄረሰብ ታጋይ፣ ዲሞክራ
ትና ታጋይ ወጣትና ሴት በሚደገፉት አቋም ላይ እንደፀና ይቆያል::

ይሁንና፣ መኢሶን በተለመው አብዮታዊ ጎዳና ለመጓዝ ተነሳስቶ እንዳለ፣ ከወዝአደሩና
ከሰፊው ታጋይ ህዝብ ቀድመው ፀረ ህዝብ ዓላማቸውን ለማረጋገጥ የሚፈልጉ ንዑስ ከበርቴ
ዎች ከውስጡ ተነሱበት:: እነዚህ ፀረ ህዝቦች "የሠራተኛ ፓርቲ" የሚለውን መጠሪያ
የፈለጉት ለስሙ ብቻ ስለሆነ፣ ከሌሎች ማርክሲስቶች ጋር ሃቀኛ የመስመርና የርዕዮተ
ዓለም ትግል አካሂደ መዋሃዱንም ሆነ፣ ከራሱ ከአብዮቱ ባለቤት ከሆነው ወዝአደርና ሰፊ
ህዝብ መዋሃዱን እንደጠር ፈሩት:: ስለሆነም፣ ስምን ብቻ በመንጠቅ በወዝአደሩ ለመነ
ገድና በኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ትግል ለማላገጥ ወሰኑ:: ነገር ግን ንቅናቄያችንን
የመከፋፈልና በእንጭጩ የመቅጨት ሴራቸው ስለከሸፈ፣ ከመኢሶን ተገንጥለው ራሳቸውን
"የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ" ብለው ሰይመው ተቋቋሙ:: እንደሚታወቀው፣ ይህ
ድርጅታቸው በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ ብቅ ብሎ ጠፍቷል:: የኢትዮጵያ ታጋይ
ትውልድ ምንጊዜም የማይረሳው ቁስል ትቶ አልፏል:: መኢሶን ግን እንኳን የዚያን ጊዜ
ቀርቶ፣ አብዮቱ ተቀጣጥሎ ይህ ነው የማይባል ድል እየተቀዳጀ ወደፊት በሚገሰግስበት
ወቅት ህልውናውን ከስምንትአመቶች የስውር ትግል በኋላ በመጋቢት 28 ቀን 1968 ዓ.ም.
ይፋ ቢያስታውቅም፣ በአቋሙ ፀንቶና የትግል መሥመሩን በግልፅ ቋንቋዎች አስፍሮ ነው::
የመኢሶንን ፕሮግራም እንጥቀሰው:—

"መኢሶን በተቋቋመበት ወቅት፣ በብዛት በአባልነት የያዛቸው አብዮታዊ ምሁ
ራን እንጂ፣ በላብአደሩም ውስጥ ሆነ፣ በጠቅላላው በሰፊው ህዝብ መሃል ገብቶ፣ ሰፊ
ቅስቀሳና የማደራጀት ጥረት አድርጎ ለመላ ኢትዮጵያ ጭቁኖች ትግል ተገቢውን አመራር
የሚሰጥ ድርጅት አልነበረም:: ይህንንም በመገንዘብ ከፓርቲ ይልቅ ራሱን ንቅናቄ ብሎ
ሰየመ:: አሁንም ቢሆን ምንም እንኳን ተጠናክሮና ከላብ አደሩና ከሰፊው ህዝብ ተዋህደ
ለትግሉ የተጣራ አመራር ለመስጠት ያደረገው ቆራጥ ተጋድሎ ብዙ ከፍተኛ ፍሬዎችን ቢያ
ስገኝም፣ አንደኛ፣ በላብ አደሩ ውስጥ የመዋሃዱ ዘመቻ ገና ብዙ ተጋድሎ እንደሚቀረው
በመመልከት፣ ሁለተኛ፣ ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም ተከታይ ቡድኖች ጋር ሃቀኛ የርዕዮተዓለም
ትግል አድርጎ፣ ከነርሱ ጋር ተዋህደ በተጣራ የፖለቲካ መሥመር የሚመራና በላብ አደሩ
መደብ ላይ የተመሠረተ ፓርቲ ለመገንባት ያለውን ፍላጎት ለማመልከት 'ንቅናቄ' የሚለውን
መጠሪያ ይዞ እንዲቆይ ተደርጓል::/የመኢሶን ፕሮግራም፣ መጋቢት 28 1968ዓ.ም./

እንወያይ፣ እንከራከር፣ እንተባበር፣ እንዋሃድ፣ ለሚለው የመኢሶን ጥሪ የከሣራው
ኢህአፓ መልስ በመኢሶን ታጋዮች፣ በግንባር ቀደም ወዝአደሮችና አርሶአደሮች፣ መለዮ
ለባሾች፣ ምሁሮች፣ በታጋይ ወጣቶችና ሴቶች ላይ የጥይት ዝናብ ማውረድ ሆነ:: ለወዝ
አደሩ ፓርቲ መፈጠር በይበልጥ ወደወዝአደሩ እንገባ ብሎ መኢሶን ለሃቀኛና ዲሞክራሲያዊ
የሠራተኞች የሙያ ማህበሮች መመሥረት ፈንታ፣ የኢህአፓ ቅጥረኞች መለስ ሲቻል ፀረ
ዲሞክራሲያዊ በሆነ ዘዴ በነዚህ ድርጅቶች አመራር ላይ ፊጥ ማለት፣ ካልተቻለም ደግሞ
እነዚህን ድርጅቶች በነጭ ሽብር ለመበተን መፍጨርጨር ሆነ:: ነገር ግን ደግሞ በዚያው
ልክ ከኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦችና በተለይ በወዝአደሩ መደብ እያደረ መንቃት የተነሳ፣
"ኢህአፓ" እየተተፋ ወደማይቀረው የታሪክ ትቢያ ወርዶ ተከሰከሰ::

የዛሬ ሶስት ዓመት በኢህአፓ ላይ የተገኘው ድል በየአጋጣሚው የሆነውን ያህል፣
በዚህ በወዝአደር ፓርቲ አፈጣጠር ጉዳይም ላይ ፀረ ህዝቡ ቡድን ይነዛ የነበረው
ውዥንብርም እየጠራ መጣ:: በሁለቱም አንፃር የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች መኢሶን
ሲጠነሰስ ጀምሮ ይታገሉለት በነበረው መሥመር ላይ ተስማምተው አቋማቸውን በይፋ ገለፁ::

የኢትዮጵያን ወዝአደሮች ፓርቲ ለመመሥረት ማርክሲስት ሌኒኒስት ቡድኖች በሃቀኛ የርዕዮተ
ዓለም ትግልና በዲሞክራሲያዊ የትግል ዘዴ ማስተባበርና ከዚያም ማዋሃድ አማራጭ የሌለው
ዘዴ እንደሆነ በይፋ ተነገረ:: በየካቲት 1969 ዓ.ም. መኢሶን በጊዜው "ማርክሲስት
ሌኒኒስት" ነን ይሉ ከነበሩት ድርጅቶች ጋር ባወጣው የጋራ መግለጫ ላይ በተከከለ
እንደሚከተለው ሠፈረ:-

"ከተለያዩ ቡድኖች በምን ዘዴ የወዝአደር ፓርቲ ለመመሥረት ይቻላል ለሚለው
ጥያቄ፣ የብዙ አገሮችን የአብዮታዊ ትግል ታሪክና የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ከመረመ
ረና ካጠና በኋላ፣ የወዝአደሩን ፓርቲ ለመፍጠር ከተለያዩት የወዝአደር ፓርቲ አመሠራረት
ዘዴዎች ፍተሻና ሳይንሳዊ የሆነው ልዩ ልዩ ማርክሲስት ሌኒኒስት ቡድኖች ኃይላቸውን
አስተባብረውና የትግል አንድነት መሥርተው በመሃከላቸው በታክቲክና በስትራቴጂ ጥያቄዎች
ላይ ሃቀኛ የሆነ የርዕዮተዓለም ትግል አካሂደው የሚዋሃዱበት ዘዴ መሆኑን አምነውበታል::"

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ለዚህ ፓርቲ መፈጠር አስፈላጊ የሆነውን ከወዝአደሩ መደብ
የመዋሃድ ጉዳይ ተገቢ ቦታውን ሰጥተውት ስለነበረ፣ በዚሁ መግለጫቸው ላይ:-

"በየፋብሪካዎቹ፣ በየማከፋፈያ ድርጅቶች በተካሄደው የከረረ ትግል በአያሌ
ፋብሪካዎች ሃቀኛ የሆነ የማህበር አመራር ያለውና በቀርቡ የተቋቋመ "የመላ ኢትዮጵያ
ሠራተኞች ማህበር" በተጠናከረ አመራር ተመስርቷል:: ድርጅት የሙያ ማህበር ጠባይ ያለው
ቢሆንም፣ ለወዝአደሩ የፖለቲካ ትግል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ ስለሚችል፣ በየደረጃው
የተመሠረቱትን የወዝአደር ማህበሮች ለማጠናከር ሰፋ ያለ የፖለቲካ ቅስቀሳ ለማካሄድና
የውይይት ክበቦች የአብዮታዊ ንቃት መድረኮች እንዲሆኑ ለመታገል..." በሚለው ከስምምነት
ላይ ተደርሶ እንደነበረ ይታወቃል::

እንግዲህ በአብዮቱ የዲሞክራሲ ዘመን ታላቁ የኢትዮጵያ አብዮት ከፊቱ የሚጋፈጡትን
ፀረ አብዮት ኃይሎች ሁሉ በማንኛውም የትግል መስክ እያጋለጠና እየመከተ ለዘላለሙ ወደ
ፊት የሚገሠግሥ ይመስል በነበረበት ወቅት፣ ምድረ የቀኝ አድርባዮች ሁሉ ያስተጋቡት
የነበረው አቋም ይህ ነበር:: በረሃም የወዝአደር ፓርቲ አፈጣጠር መንገድ ይኸው ነበር::
ትክክለናውም የአብዮቱ ፋና ይህ ነበር::

ዛሬ ግን የአብዮታዊው ማዕከል ጥንስስ "ኢማሌድህ፣ ሳይፈላ ተደፍቶ"፣ ሳይከካ
የተቦካ ሌላ የፀረ አብዮት ማዕከል ተተክቷል:: ይህ "አዲሱ ጥንስስ" ወይንም "ማዕ
ከሉ" ወይንም "ኮሚሽኑ" ወይንም "የማጣሪያ ቢሮ"... ወዘተ የተፈጠረው፣ ከዛሬ
ሁለት ዓመት ተኩል በፊት የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች በይፋ የተለሙትን፣ ከዚያም
የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች ሁሉ ተራ በተራ እየተንጠባጠቡ የከዱትን የወዝአደር ፓርቲ
አፈጣጠር ዘዴ ተከተሉ ሳይሆን እሱን ተፃር ነው:: ይህ ፀረ ወዝአደር፣ ፀረ ህዝብና
ፀረ አብዮት ጎዳና ደግሞ፣ በጠቅላላው በሃገራችን የፀረ አብዮት ኃይሎችን ማየልና
የውጭ ኃይሎችን ባገራችን ላይ መንገሥ ተከተሉ በፀረ አብዮት ፋና እየተጋገዘ የመጣና
እዚህ የደረሰ ሂደት ነው:: በታጋዮች ደም ተራ በተራ የተገኙትን የአብዮታችንን
ድሎች ከሰፊው ሕዝብ እጅ እየፈለቀቁና እንዳልነበሩ አድርጎ ማውደም የያዘው የቀኝ
ኃይሎች ህብረት፣ ዛሬ ሥልጣኑን ወደማደላደል እያመራ ይህንን "ኮሚሽን" የተባለ ስመ
ጥሩ "ማዕከል" ሲያውጅ፣ በዚያው በፀረ ወዝአደርና ፀረ ህዝብ ጎዳናው ወደፊት መራ
መዱን እንጂ፣ ከፀረ አብዮት አፋፍ ተመልሶ ወደአብዮቱና ወዳጆቹ ሠፈር መዋሃዱ አይደለም::

ነገር ግን ይህንን ክፍል ከመዝጋታችን በፊት ደግሞ፣ ስለ "ኮሚሽኑ" ወይንም
ስለ "ማዕከሉ" ወይንም ስለ "ማጣሪያው ቢሮ" መፈጠር በሚነገረው ዓይን ያወጣ
ሸፍጥ ላይ መመለስ አስፈላጊ ነው:: በዕውነት ይህንን ፀረ ወዝአደር፣ ፀረ ህዝብና
ፀረ አብዮት "የሠርቶ አደር ፓርቲ" ለመመሥረት ያሰፈሰፉት ኃይሎች በገሃድ ያለውን
ነገር ለመሸፈጥ ዓይናቸውን እንኳን አያሹም:: እስቲ እንመልከተው:-

እነሱ አሁን ደግሞ እንደሚሉት ከሆነ:- "በየትኛውም የኮሙኒስቶች ንቅናቄ ታሪክ፣
ከራሺያ እስከ ቪየትናም አብዮት፣ የፓርቲ አመሠራረት በጅምላ /?/ የድርጅቶች ወይም
የግለሰቦች መገጣጠም ወይም መቀላቀል ሳይሆን በመሠረቱ የታጋይ ኮሙኒስቶች አንድነት
ነው:: የኢማሌድህን የህብረት ሂደት ስንመለከተው ግን፣ መሠረታዊ ሃሳቡ የኮሙኒስቶችን
አንድነት ዕውን ለማድረግ ሳይሆን፣ መካኒካል በሆነ መንገድ /?/ ድርጅቶችን በጅምላ/?/
በመገጣጠም "ፓርቲ" ለመመሥረት ነበር:: ስለዚህም፣ ኢማሌድህ ውስጥ የነበሩ የእነ
መኢሶንና ኢጭአት መንሸራተት፣ መፈርጠጥ ወይንም መፍረክረክ መሆን ነበረበት/../"
/ህብረት ድምጽ ቁ.6፣ ገጽ 4-5 ግንቦት 1971/

"ከራሺያ እስከ ቪየትናም"፣ "በመሠረቱ" "መካኒካል በሆነ መንገድ" ...
ወዘተ:: በዕውነቱ ተላልቀና የበለሆች ቃላት ናቸው:: ሲባል ተሰምቷል:: የሚያሳዝነው
ግን ባዶ ገለጣዎች መሆናቸው ነው::

እንደዕውነቱም ከሆነ ይሄንን ዝባዝንኬ እናም መተቸት አያስፈልገንም:: እን
ባቢው በዛው በህብረት ድምጽ መጽሔት ቁጥር 5 ላይ የተፃፈውን አንጓ በዚህ ጽሑፍ
ውስጥ ከዚህ በላይ የጠቀስነውን አንቀጽና አሁን ደግሞ ከዚያው ከህብረት ድምጽ ቁ.6
የጠቀስነውን አንቀጽ አስተያይቶ ፍርዱን ይስጥ ብለን ልናልፈው እንችላለን:: ብቻ
እንዳው "የኮሚሽኑና የማዕከል" ደብሮች ሆነው የተነሱትን ኃይሎች ለነገሩ ያህል

እንጠይቃቸውና፣ ለመሆኑ የሠርቶ አደሩን ፓርቲ የሚያክል ነገር "ድርጅቶችን ወይም ግለሰቦችን በጅምላ፣ ሜካኒካል በሆነ መንገድ በመገጣጠም ወይም በመቀላቀል" ለመፍጠር ይቻላል የሚለው "መሠረታዊ ሃሳብ" የቀረበው የትና መቼ ነው? በየትኛው ጽሑፍና በየትኛው የቀሰቀሳ መድረክ ነው?

ክቡራን "ጓዶች"! የታወቀውን መድገም አይሁንብንና የሠራተኛው ፓርቲ "መሠረታዊ" ድርጅታዊ መርህ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ነው:: የዚህን ሁሉ የቀጠረ ማንም ሰው ቢሆን፣ "ድርጅቶችን ወይም ግለሰቦችን በጅምላና ሜካኒካል በሆነ መንገድ በማገጣጠም ወይም በመቀላቀል" የሠራተኛውን ፓርቲ የሚያክል ነገር ሊፈጥር ይችላል ብሎ አይናገርም:: በዚህ ማንንም ለማታለል አይቻልም:: "ተንሸራተቱ" ፣ "ፈረጠጡ" ፣ "ተፍረከረኩ" የሚባሉልን ድርጅቶችም፣ እንኳን ዛሬ ቀርቶ፣ ከዛሬ አስራ አንድ ዓመት በፊት ከተናገርነውና ከጻፍነው የቅንጣት ያህል ዝንፍ አላልንም:: የወዝአደሩ ፓርቲ እንዳች ዓይነት ኮን—ፌዴሬሽን እንዳልሆነ የምናውቀው ዛሬ አይደለም:: ዛሬም የምንለው ዕውነተኛው ፓርቲ የሚፈጠረው፣ በማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች መካከል በእኩልነት መድረክ ላይ ነፃና ዲሞክራሲያዊ የሆኑ የርዕዮተ ዓለም፣ የፖለቲካ መሥመር፣ የፖለቲካና የስትራቴጂ ውይይቶች ሲካሄዱ ነው:: እያንዳንዱ ድርጅት የሌላውን ድርጅት ነፃ ህልውና ተቀብሎ አክብሮ ቀንና የእኩልነት ህብረት ሲመሠረት ነው:: ደግሞም፣ ጀንበር በጠለቀች ቁጥር አቋሙን መለዋወጥ ሲያበቃ ነው:: እንደዚህ በዲሞክራሲ፣ በእኩልነት፣ በመከባበርና በፅናት ላይ የተመሠረተ ህብረት፣ ህያው በሆነ የጋራ ትግል፣ ህያው በሆነ መፈቃቀር ይተሳሰራል:: እያንዳንዱም የራሱን ድርጅት ህልውና ፈለገ ፈቀደ እንዲያከትም ለማድረግ ዝግጁ ይሆናል:: አያን ይቀሃል:: የወዝአደሩን ፓርቲ በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርሆዎች ይመሠረታል::

እንግዲህ እስቲ "ተንሸራተቱ" ፣ "ፈረጠጡ" ፣ "ተፍረከረኩ" የሚሏቸውን መኢሶንንና ኢጭአትን ለጊዜው ወደ ጐን እንተዋቸውና፣ እረ ለመሆኑ "ኢማሌድህ መድረክ ላይ ጸንተው ቆዩ" የሚባሉላቸውን "ማሌሪድ፣ ሰደድና ሊግ" የበላቸው ምንድን ነው? ወዝ ሊግ እንደሚለው፣ ፈለገውና ፈቀደው "እድሜያቸውን አሳጠሩ"! በበኩላችን መልሱን በቁጥር 70 ላይ ሰጥተናል:: እንመለስበትም::

ይሁንና፣ የወዝአደሩ ፓርቲ የሚመሠረተው "ድርጅቶችን ወይም ግለሰቦችን በጅምላና ሜካኒካል በሆነ መንገድ በማገጣጠም ወይም በማቀላቀል አይደለም" ከተባለልን አይቀር፣ ይሄንን "ከህብረት ድምፅ" መጽሔት የምንጠቅሰውን ጉደኛ "ስምምነት" ምን አመጣው? በዕውነቱ እንደሚባለው ማርክስና ሌኒን በመቃብራቸው ውስጥ እየተገላበጡ ናቸው:: አንባቢም እንደኛው አንብቦ "ጉድ" ይበል:: ይሄውና:— /ይሄ ጉደኛ "ስምምነት" ራሳቸውን ቀስቅሶ አላሳርፍ ብሏቸዋል::/

"1. የወዝአደሩን ፓርቲ ለማስገኘት /የሚቻለው/... በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮተዓለም የታጠቁትን ዕውነተኛ ታጋዮች /ግለሰቦች "የና"/ በማዋሃድ ነው::"

"3. ፓርቲውን ለመፍጠር በቅድሚያ በአብዮታዊ ትሉታቸውና አስተዋፅኦቸው /ሚሪት/ ከኢማሌድህ አባል ድርጅቶችና መመዘኛውን /የግለሰብ "የና"/ የሚያሟላ ከተገኙ ከአባል ድርጅቶችም ውጭ የሚገቡበት መዓከል መመሥረት አስፈላጊ ነው::"

"4. ይህ... ማዕከል በአብዮታዊው መመዘኛ መሠረት ለኢማሌድህ አባል ድርጅቶች አባላት ቅድሚያ በመስጠት የፓርቲ አባላትን /ግለሰቦችን "የና"/ ይመለምላል::

/"የህብረት ድምፅ" ቁ.5፣ ገጽ 16–17 የካቲት 1971/

ከዚህስ በኋላ?

"ስምምነት" በጥሩና በከባዱ ቋንቋ እንደሚለው ከሆነ፣ ከዚህ በኋላ "ማዕከሉ ፓርቲውን ያዋቅራል":: ይሁንና፣ እና ደግሞ በቀላሉ እንናገረውና፣ "የመለመላቸውን" ግለሰቦች "አያገጣጠመ ያቀላቅላል" እንበል:: ሌላ መንገድ የለውም:: "...ሳታመሃኝ ብላኝ" ነው?

አይ "አብዮታዊ ሰደድ" "ቀኞች የሚናገሩትና የሚሠሩት፣ የሚጽፉትና ወደተግባር የሚተረጉሙት ሁሉ ለየቅሉ ነው" ይበል? በተለይም የወዝአደሩን ፓርቲ በሚመለከተው ጉዳይ ላይ ደበስባሳና ሙልጭልጭ አቋም ይወስዳሉ" ይበል? "በልዩ ልዩ ጽሑፎቻቸው እንደ እስስት የሚቀያየሩ መንደርደሪያዎች ይኖራቸዋል" ይበል? እናን "ቀኝ መንገደኞች" መንካት እክ ነው:: ጉድ ነው!!

ብቻ ደግሞ ከመጨረሳችን በፊት፣ ዛሬ ለመጨረሻው ጊዜም ባይሆን፣ ከዚህ የወዝአደር ፓርቲ ጥያቄ ላይ ያለፉት ሁለት ዓመታት ያዩትን የፀረ እውነተኛ ወዝአደር ፓርቲ ዘመቻ ባጭሩ እንመለስበትና እንባቢን አንዳንድ ቁም ነገሮችን እናስታውሰው::

የቀኝ ኃይሎች ህብረት ይህንን ፀረ ወዝአደር ሂደት ሲጀምር በመጀመሪያ በስንት መከራ የተገኘውን የተራማጆች ህብረት ማፍረስ ጀመረ:: የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ድርጅቶች ሃቀኛ የሆነ የርዕዮተ ዓለምና የፖለቲካ መሥመር ትግል በመካከላቸው አካሂደው ወደውህደት እንዳይሸጋገሩ ዲሞክራሲያዊ ውይይቶችን አፈነ:: ለዚህ ውይይት አመቺ ሁኔታ ሊፈጥሩ የሚችሉት ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲዳበሩ ከማድረግ ፈንታ፣ ይባሱኑ ደብዛቸውን አጠፋቸው:: ምንም እንኳን ለአብዮታችን ወደፊት መራመድ የሚቀረቀሩ

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጭቁኖች ከዳር እስከዳር ያስተጋቡት የነበረውን "የወዝአደር ፓርቲ ባስቸኳይ ይመሥረት"፣ "የተራማጆች ህብረት ይጠንከር"፣ "ኢማሌድህ ከህብረት ወደ ውህደት ይሸጋገር" የሚሉትን መፈክሮች ቀለበስ ቢያስተጋባም፣ በይፋ ድርጊት የሚፈጸመው የዚህን ተቃራኒ ነበር:: ስለሆነም፣ እነዚህን መፈክሮች ከሰፊው ሕዝብ ተደባልቀው እያስተጋቡ የዲሞክራሲ መብቶችን መለቀቅ መቃወም፣ "የሠራተኛውን ፓርቲ" ባቋራጭ ለመመሥረትና በኢትዮጵያ ጭቁኖች ትከሻ ላይ ለመፈናጠጥ የታሰበ የከሃዲ ንዑስ ከበርቴያችና የአድሃሪው ቢሮክራሲ ሴራ መሆኑን መኢሶን አስገነዘበ:: በሰሀዴ ቁ.65 በጥር ወር 1970 ዓ.ም. እንዳስቀመጠው:—

"አድርባዮች፣ ንዑስ ከበርቴው መደብና አድሃሪው ቢሮክራሲ ይህንን መፈክር ሲያስተጋቡ ወደሃቀኛ የወዝአደር ፓርቲ ቶሎ ቶሎ እንራመድ ሳይሆን፣ የናን ህብረት የሚያንጸባርቅ "የወዝአደር ፓርቲ" ባቋራጭ ከወዝአደሩ ቀድመን እንመሥርት ማለታቸው ነው:: "ባስቸኳይ" ሲሉ "ባቋራጭ" ማለታቸው ስለሆነ፣ ለንቃት፣ ለድርጅትና ለትጥቅ አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩትን፣ ሃቀኛ የወዝአደር ፓርቲ ባስቸኳይ ለመመሥረት የሚረዱትን ዲሞክራሲያዊ መብቶች አሁኑኑ መለቀቅ ይቃወማሉ:: ስለሆነም፣ የወዝአደር ፓርቲ ባስቸኳይ ይመሥረት ከሚለው መፈክር ተነስተን፣ እና ቶሎ ቶሎ እንራመድ ስንል፣ እነሱ ደግሞ "ባቋራጭ" እንራመድ ሲሉ፣ በመሃከላችን ያለው ትግል የለየለት የመደቦች ትግል ነው:: ጥያቄው የወዝአደር ፓርቲ እንዴት ይመሥረት የሚል ጥያቄ አይደለም::"

ከዚህ በኋላ የሆነውን ሁሉ ሁላችንም እናውቀዋለን:: "ከህብረት ወደ ውህደት ይሸጋገር" ይባልለት የነበረው ኢማሌድህ፣ ለኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች የጋራ ትግል፣ የሃቀኛ የርዕዮተ ዓለም ትግልና ወደውህደት መሸጋገሪያ መድረክ መሆኑ ቀርቶ፣ ከአባል ድርጅቶች እየተራቀቀ፣ በፖለቲካ መሥመሩ ከኪሣራ ወደኪሣራ እየተደፋ ወደታሪክ አተላነት ዘቀጠ:: በቀኝ ኃይሎች ህብረት ውስጥ እያየለ የመጣው አድሃሪ የሲቪልና የሚሊቴሪ ቢሮክራሲ፣ በቀኝ አድርባይ ድርጅቶች ፊታውራሪነትና በነለገሠ አሰፋው ሸረና ክሊክ አስፈፃሚነት የአብዮቱን ሠፈር ካጠቃና ካዳከመ በኋላ፣ ኢማሌድህን በአዋጅ አፈረሰው::አንድ ትውልድ ያፈራቸውን ማርክሲስት ሌኒኒስቶችና ግንባር ቀደም ወዝአደሮች በየሥፍራው ረሽኖና በየእሥር ቤት አጉሮ "ያጠናቀቀ" ሲመስለው፣ ከኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ወዝአደሮች፣ አብዮታዊ ምሁራንና መለዮ ለባሾች ውጭ፣ ራሱን "የሠርቶአደር ፓርቲ" ብሎ ለመሰየም እስከስታ እየወረደ መጣ::

ነገር ግን ይህ "የሠርቶአደር ፓርቲ" የሚታወጅበት ቀን እንደተነገረን ከሆነ "ሩቅም" ባይሆን ገና ነው:: ዛሬ "ሠርገኛ ደረሰ በርበሬ ቀንጥሱ" እየተባለ ነው:: ለዚህም ምክኒያቱ የስልጣን ሽኩቻውና አሸቅዳምዳሚው ገና ያልተረጋጋ በመሆኑ ነው:: በዚህ ሽኩቻ ውስጥ፣ ባንድ በኩል ፍፀም ከሃዲውና የስልጣን ጥም ያናወዘው የነለገሠ ክሊክ አለ:: በሌላው በኩል፣ ይህንን ክሊክ ለማዳከም ሲል በተሰበጣጠሩ ምክኒያቶች ለጊዜው የተቀሳሰፈው የከፍተኛ መኮንኖችና ሲቪል ቢሮክራቶች ክንፍ አለ:: በነዚህ ሁለት ክንፎች መሃከል የሰነበተው ገብገብ፣ ሽኩቻና ኢንትሪግ በኮሚሽኑ መቋቋሚያ ዋዜማ የታየውን ያህል ከዚያም ወዲህ፣ "የሠርቶ አደር" ፓርቲያቸውንም ሲወልዱ እስኪለይለት መቀየቱ የማይቀር ነው:: የመጀመሪያው በተለይ፣ በኢማሌድህ ምርኩዝ ያደረገው ጉዞ ቢቀጭበትም ሌሎች የውጭ ኃይል ጣልቃገብነትን ጨምሮ፣ ያጠመዳቸው ተንኮሎችና መንገዶች እንዳሉ ብዙ ምልክቶች እየታዩ ናቸው:: ወደፊት ገሃድ ይታያሉ::ያለፈው ሰሞን የነታምራት/እንዳለ ትርዒትም የዚሁ ነፀብራቅ መሆኑ እንጅ፣ ሌላ ትርጉም የለውም:: እዚሁ ላይ መነገር ያለበት ሌላው መሠረታዊ ጉዳይ ግን፣ በዚህ በኋለኛው ክፍል ውስጥ ዛሬም ቢሆን አገር ወዳድና ዲሞክራት የሆኑ ግለሰቦች እንዳሉና አንዳንዶቹም በሁኔታዎች ተገደው የተቀላቀሉት እንደሆነ ነው:: መኢሶን፣ ዛሬ ይህንን ስመጥሩ "ኮሚሽን" እየተቃወመ አቋሙን የሚገልጸው ፍፀም ዕውር በመሆን ሁኔታዎችን በስሜታዊነት በመመልከት አይደለም:: ይልቁኑ የያንዳንዱን ጉዳይ ነባራዊ ሀልዎና ከስሜትና ከቂም በቀል ውጭ እየመረመረና እያጠና ነው:: እንደዕውነቱ ከሆነ፣ መኢሶን ማለትም ይህ ነው::

ስለሆነም፣ መኢሶን ዛሬም እንደገና ዕውነተኛ የወዝአደር ፓርቲ እንዲፈጠር፣ ሃቀኛ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ሁሉ በዲሞክራሲያዊ የትግልና የአንድነት መድረክ ላይ እንተባበር፣ ተባብረንም ፈልገንና ፈቅደን የየራሳችን ድርጅቶች ህልውና እንዲያከትም በማድረግ እንዋሃድና ዕውነተኛውን የወዝአደሩ ፓርቲ እንመሥርት እያለ ድምፁን ከፍ አድርጎ ያሰማል::

የኢትዮጵያ ሃቀኛ ማርክሲስት ሌኒኒስቶችና ግንባር ቀደም ወዝአደሮች ሆይ!

ስመጥሩዉ ኢህአፓ በንዑስ ከበርቴ ቀብጥብጥነትና የግራ አድርባይነት በአብዮታችን፣ በዚሁች በውድ አገራችንና በታጋዩ የኢትዮጵያ ትውልድ ላይ የፈጸመውን ገፍ አይታችኋል:: ይህ ነፍሰ ገዳይ ድርጅት ስንቱን ታጋይ ምሁር፣ ወዝአደር፣ አርሶአደር፣ መለዮ ለባሽ፣ የጭቁን ብሄረሰብ ታጋይ፣ አገር ወዳድ፣ ዲሞክራት፣ ወጣት፣ ሴት... ረሽኖ አስረሽኖ አልፏል:: ይሁንና ከኢህአፓም በኋላ ሌላዉ የንዑስ ከበርቴ ትምክህተኛና የቀኝ አድርባይ ክንፍ ደግሞ፣ እንደዚሁ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ስም እየማለና እየተገዘተ የፈጸመውንና ታሪክ የማይረሳውን ይህ ነው የማይባል የግድያ፣ የእሥራትና የክህደት ዘመቻ አይታችኋል::

ከንግዲህም "ከድብሰበስና መሙለጥለጡ" የሃገሪቱን ታጋዮች መጨፍጨፍና ማስጨፍጨፉ፣ ከአፍንጫ አሻገር ባለመመልከት መጠቆሙና ማስጠቆሙ ለፀረ አብዮት መሥራት ብቻ እንደሆነ፣ ለመጨረሻው ጊዜ እንዲተረዱት ያስፈልጋል:: ይልቁኑ በሰፊው ህዝብ ድምፅ ቁጥር 69 ባደረገነው ጥሪ መሠረት እንደሁኔታው እየተገናኛችሁ ተወያዩ:: በህቡዕ ተሳሰሩ:: ተደራጁ:: አደራጁ:: ከቂም በቀል ርቃችሁ ተሰባሰቡ:: መጭው ጊዜ ብሩህ ነው:: ዐውነተኛው የወዝአደር ፓርቲ የሚፈጠርበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም::

በየትኛውም የህብረተሰቡ ክፍልና የሥራ መስክ ያላችሁት የኢትዮጵያ አገር ወዳድና ዲሞክራቶች ሆይ !

እና የመኢሶን ታጋዮች ፀንተን የቆምነው በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ ነው:: ይህ መድረክ የአገር ወዳዶቻችንና የዲሞክራቶቻችን በነፃ የመደራጀት መብት ይፈቅዳል:: እስካሁን "ማርክሲስት" ብትሆኑም ባትሆኑም "ማርክሲዝም፣ ሶሻሊዝም" እያላችሁ ብዙ ስትናገሩ፣ ብዙ ስትሠሩ አይተናል:: ይልቁኑ ማንነታችሁን በሃቀ ጠብቃችሁ፣ በአገር ወዳድና በዲሞክራትነታችሁ ተደራጁ:: በተለይ ዛሬ የአብዮታችን የዲሞክራሲ ዘመን አክትሞ፣ ፀረ ዲሞክራሲ በነገሠበት ዘመን፣ የውዱ ሃገራችን ብሄራዊ ክብር ተገሥሶ፣ ብሄራዊ ውርደትን በተከናነበበት ወቅት የናንተ መደራጀት እንደህይወት እስትንፋስ ያስፈልጋል:: የትግላችን መድረክ ሰፊ ነው:: ይህቺ ውድ አገራችን የጀግና አገር ወዳዶችና ዲሞክራቶች አገር ናት:: የዛሬው አገር ወዳድና ዲሞክራት ትውልድ ይህንን የምንኩራበትን ታሪክ ዓይኑን ጨፍኖ ለመርሳት የተዘጋጀና የዳሸቀ ትውልድ መሆን የለበትም:: እንዲያውም ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ከፍተኛ የታሪክ ግዴታና ሃላፊነት ያለበት ትውልድ ነው::

በየትም ሥፍራ ለምትዋደቁ የኢትዮጵያ ጭቁን ብሄረሰቦች ታጋዮች ሆይ !

በብሄረሰቦች እኩልነት ያሸበረቀች አዲሲቱ ኢትዮጵያ የምትመሠረተው ብሄረሰቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ለመወሰን ያላቸው ሙሉ መብት የታወቀ፣ የተረጋገጠና የተከበረ ሲሆን ነው:: የብሄረሰቦቿ አንድነት በእኩልነትና በመከባበር መርሆች መሠረት ሲመሠረትና ሲደረጅ ነው:: ነገር ግን ለዚህ ቅዱስ ግብ፣ ከየትኛውም ብሄረሰብ ይሁን ከየትኛው፣ ይህቺ አገር ያበቀለቻቸው የጨቋኝና የተጭቋኝ ብሄረሰቦች ታጋዮች ሁሉ መተባበር አለባቸው:: እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደ ነፃነትና ዲሞክራሲ፣ ወደእኩልነትና መከባበር መጓዝ አለባቸው:: ስለሆነም፣ መኢሶን ዛሬም መሰቦ ባንዱ በኩል ትምክህተኝነትን፣ በሌላው በኩል ጠባብ ብሄረተኝነትን በጋራ እየተዋጋን በነፃነትና በዲሞክራሲ የትግል ጎዳና ላይ እንገፋ እያለ ከየትኛውም ብሄረሰብ ለሚመጡ ታጋዮች ሁሉ ድምፁን ከፍ አድርጎ ያሰማል:: መኢሶን ዛሬ ትምክህተኝነት ነገሰ ታሪካችን አይቶት በማያውቀው መጠንና ስፋት በሲዳሞ፣ በባሌ፣ በወለጋ፣ በሐረርጌ፣ በአርሲ፣ በትግራይ፣ በኤርትራና በሌሎችም ጭቁን ብሄረሰቦች ላይ የሚወርደውን ጭፍጨፋና ግፍ የተመላበት አመጽ እያወገዘ፣ ለዕውነተኛ እኩልነት ከቆሙ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር ሁሉ ለመተባበር ያለውን ፍላጎትና ጥሪም በዚሁ አጋጣሚ ለጭቁን ብሄረሰቦች አብዮታዊ ታጋዮች ሁሉ ያድስላቸዋል::

እንግዲህ ትግሉ ያሻውን ጊዜ ይወስዳል እንጂ፣ ያሻውን መስዋዕትነት ይጠይቃል እንጂ፣ ያሻውን ያህል መራራ ይሆናል እንጂ፣ ያሻውን ያህል ውስብስብና ከባድ ይሆናል እንጂ፣ ያሻውን ያህል ትዕግስት ይጠይቃል እንጂ፣ ኢትዮጵያችንን በሚወዷት ቀናተኛ በሆኑት ልጆቿ የተባበረ ትግል:- በህዝባዊነቷ ደምቃ፣ በዲሞክራሲያዊነቷ ፈክታ፣ በብሄረሰቦቿ እኩልነት አሸብርቃ፣ በብሄራዊ ነፃነቷ ኮርታ፣ በህዝቦቿ ታታሪነት በልፀጋና አብባ እንደምናያት ከቶም አንጠራጠርም:: ድሉ የሰፊው ህዝብ ነው:: ትግሉ ይቀጥላል::

- ሃቀኛ ማርክሲስቶች፣ ዲሞክራቶች፣ አገር ወዳዶች፣ የጭቁን ብሄረሰቦች አብዮታዊ ታጋዮች ትግላችሁን አስተባብሩ!
- ለዲሞክራሲና ለብሄራዊ ነፃነት ትግሉ ይቀጥላል!
- የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ የህዝብ ትግል ያሸንፋል::